-------------------------------

**መመሪያ ቁጥር 890/2014**

**የሲሚንቶ ግብአት እና የሲሚንቶ ምርት ጥራትን ለመቆጣጠር የወጣ የማዕድን ሚኒስቴር መመሪያ**

-------------------------------------------------------

**መግቢያ**

ሲሚንቶ ለማምረት ፈቃድ ወስደው ወደ ስራ ለገቡና ለሚገቡ የሲሚንቶ አምራቾች ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ የሚያጋጥማቸውን ችግሮች መለየት እና መፍታት እንዲሁም በሙሉ አቅማቸው የሚያመርቱበትን ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የሲሚንቶ ምርት ምርታማነት እና ጥራት ከፍ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ለሲሚንቶ ምርት ግብዓት የሚሆኑ ማዕድናት በሚመረቱባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎችን የልማት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በማስፈለጉ፤

በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 አንቀጽ 23 እና በማዕድን ስራዎች አዋጅ ቁጥር 678/2002 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 82 (2) መሰረት ይህ መመሪያ ወጥተዋል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "**የሲሚንቶ ምርትና ግብአት መቆጣጠሪያ መመሪያ ቁጥር 890/2014**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጉም**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1/ ‹‹ፋብሪካ›› ማለት የፀና ፈቃድ ያለውና

-------------------------------------------------------------------------------

**Directive No. 890/2022**

**Ministry of Mines Directive to control the quality of Cement input and cements production**

-------------------------------------------------------

**Preamble**

WHEREAS it is necessary to supervise and support Cement factories that have been granted a license and commence production, to identify the problems they encounter and resolve such difficulties as well as create suitable conditions for them to utilize their full capacity and enhance the cement productivity and quality.

WHEREAS it is necessary to ensure the benefit of residents found at locations whereby the input minerals for cement are produced.

NOW, THEREFORE, this Directive is issued pursuant to Article 23 of the Proclamation No.1263/2021 and Mining Operation Proclamation No. 678/2010 (as amended) Article 82 (2).

**Part One**

**General**

**1. Short Title**

This directive may be cited as the "**Cement Production and Inputs Control Directive Number 890/2022**."

**2. Definitions**

In this directive, unless the context otherwise requires:

1/ "Factory" means a cement manufacturing

ሲሚንቶ የሚያመርት ድርጅት ነው፤

2/ ‹‹ግብዓት አቅራቢ›› ማለት ማዕድንን በማምረት ለሲሚንቶ ፋብሪካ ግብዓት የሚያቀርብ የማዕድን ማምረት ባለፈቃድ ነው፤

3/ ‹‹የግብዓት የሽያጭ ዋጋ›› ማለት ለሲሚንቶ ምርት በግብዓትነት የሚውሉ ማዕድናት የማምረት እና የትራንስፖርት ዋጋን ሳይጨምር በሚኒስቴሩ የሚተመን ዋጋ ነው፤

4/ ‹‹ግብዓት›› ማለት ለሲሚንቶ ምርት የሚውል ማዕድን ነው፤

5/ ‹‹ክሊንከር›› ማለት በከፍተኛ ሙቀት የተቃጠለና ለሲሚንቶ ምርት ዝግጁ የሆነ ግብአት ነው፤

6/ ‹‹አግባብነት ያለው አካል›› ማለት የማዕድን ሚኒስቴር ወይም በክልል የማዕድን ሥራዎችን ለማስተዳደር በሕግ ስልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

7/ ‹‹ክልል›› ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47(1) የተገለጹትንና በአንቀጽ 47 (2) እና (3) መሠረት የተቋቋሙ ክልሎችን እንዲሁም የአዲስ አበባና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

8/ ‹‹ሰው›› ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

9/ "ፈቃድ ሰጪው ባለስልጣን" ማለት የማዕድን ሚኒስቴር ወይም የክልል የማዕድን ስራ ፈቃድ የመስጠት ሀላፊነት ያለው አካል ማለት ነው፤

10/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

factory that has a valid license;

2/ "Input Supplier" means a licensee that produces and supplies input minerals to cement factories;

3/ "Sales Price of Inputs " means a sales price of cement input minerals to be determined by the Ministry, excluding the cost of production and transportation;

4/ "Input" means a mineral that will be used for cement production;

5/ "Clinker" means an input burned at high temperature and is ready for cement production;

6/ "Relevant Body" means the Ministry of Mines or the legally authorized regional body that administers mining operations;

7/ "State" means any state specified under Article 47(1) and established pursuant to article 47(2) and (3) of the FDRE constitution, and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City Administrations;

8/ "Person" means any natural person or a legal entity;

9/ "Licensing authority" means the ministry of mines or state organ in charge of the mining sector as appropriate;

10/ Any expression in the masculine gender includes the feminine.

**3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በኢትዮጲያ ውስጥ በሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች እና የሲሚንቶ ግብዓት ማዕድናትን አምርተው ለፋብሪካ በሚያቀርቡ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የመንግስት አካላት ተግባር እና ሀላፊነት

**4. የማዕድን ሚኒስቴር**

1/ ለፋብሪካዎች፤

ሀ/ ለሲሚንቶ ምርት የሚያገለግሉ የማዕድናት ግብዓቶችን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

ለ/ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፤

ሐ/ የሚያስፈልጉ መለዋወጫ እቃዎችን በሚያስፈልገው መጠን እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፤

2/ የሲሚንቶ እና የሲሚንቶ ምርት ግብዓት ማዕድናት የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3/ ፋብሪካዎች በገቡት የውል ግዴታና የስራ ፕሮግራም መሰረት መስራታቸውን ይከታተላል፤

4/ የፋብሪካዎችን ምርታማነት ለማሳደግ የድጋፍ ስራ ይሰራል፤

5/ የሲሚንቶ ግብዓት ማዕድናትን ዋጋ ይተምናል፣ በተመኑ መሰረት ግብይት እንዲፈፀም ያደርጋል፤

6/ የፋብሪካዎች የምርት እቅድ እና የሥራ አፈጻጸም ይገመግማል፤ የክትትል እና የቁጥጥር ተግባራት በማከናወን አስፈላጊ የማስተካከያ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

**3. Scope of Application**

This directive shall apply to cement factories and input suppliers that operate within the territory of Ethiopia.

## Part Two
## The Functions and Responsibilities of Government Bodies

**4. Ministry of Mines**

1/ To Factories;

A. provide support to acquire input minerals used for cement production;

B. work in cooperation with the concerned bodies to bring industrial peace;

C. Provide support to get the necessary spare parts at the required amount.

2/ Ensure that the produced cement and input minerals fulfill the necessary quality standards;

3/ inspect whether the factories carry out their operations in line with their contractual obligations and work plan;

4/ provide support to enhance the productivity of factories;

5/ determine the price of input minerals; ensure that transactions are carried out in line with the price that has been set;

6/ evaluate the production plan and performance of factories; undertake the necessary remedial measures by performing monitoring and control activities;

7/ ለሰጠው ፈቃድ የግብዓት ማዕድናት የክምችት መጠን ኦዲት ያደርጋል፣ በግኝቱ መሰረት ቀጣይ አስፈላጊ ተግባራትን ያከናውናል፤

8/ ለመንግስት የሚከፈሉ ክፍያዎች መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፤

9/ በፋብሪካዎች፣ በግብዓት ማዕድን አምራቾች እና በአካባቢው ማህበረሰብ መካከል መልካም ግንኙነት እንዲኖር ይሰራል፤

10/ የፋብሪካዎች እና የግብዓት ማዕድናት አምራቾችን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ የአቅም ግንባታ ስራዎች እንዲሰሩ ድጋፍ ያደርጋል፤

11/ ሲሚንቶ እና የግብዓት ማዕድናት የሚመረትባቸው አካባቢዎች የተሻለ የመሰረተ ልማት እና የሃይል አቅርቦት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

12/ ያለበቂ ምክንያት ከአቅም በታች የሚያመርቱ ወይም ማምረት ያቆሙ የሲሚንቶ እና የግብዓት አምራቾችን በመለየት ድጋፍ ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱም የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

13/ በዘርፉ የስራ እድል እንዲፈጠር እና የማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ከሚለከተው አካል ጋር ተባብሮ ይሰራል፤

14/ ይህንን መመሪያ በማያከብሩ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣ እንዳስፈላጊነቱ ከሚመለከተው አካል ጋር

7/ audit the stock amount of input minerals for the licenses that have been issued; carry out subsequent necessary actions based on the findings;

8/ ensure the necessary payments are effected to the government;

9/ work to create good relations among factories, input mineral producers and the surrounding community;

10/ provide support for capacity building works that enhance the capacity of factories and input mineral producers;

11/ Create favorable conditions for better infrastructure and power supply in areas where cement and input minerals are produced;

12/ Identify, and provide support to factories and input suppliers that are producing below capacity or ceased production for no apparent reason; undertake corrective measures as necessary;

13/ Work in cooperation with the concerned body in order to create work opportunities within the sector and to ensure the economic benefit of the society;

14/ take administrative measures against those who do not comply with this directive;

በመተባበር ህጋዊ እርምጃዎችን ያስወስዳል፤

15/ ምርታማነትን ለማሳደግ ለዘርፉ ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

5. የክልል ስልጣንና ተግባር

በክልል የማዕድን ሥራዎችን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው አካል የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤

1/ የግብአት ማዕድናት ማምረቻ ቦታዎችን ይለያል፤

2/ በሕግ አግባብ ለተደራጀ የግብአት አምራች ባለፈቃድ የምርት ቦታን በውል ያስረክባል፤ ያስተዳድራል እንዲሁም ጊዜው ሲጠናቀቅ ውሉን አቋርጦ ይረከባል፤

3/ የግብአት አምራች ባለ ፈቃድ የአከባቢ መልሶ ማልማት ስራ መስራቱን ይቆጣጠራል፤

4/ የግብአት አመራረት፣ ጥራት ማስጠበቅና የአካባቢ መልሶ ማልማት ላይ ስልጠና ይሰጣል፤

5/ የግብአት ማዕድናት አምራችቾች የሚያቀርቧቸው ሰነዶችን ይሰበስባል፤ ትክክለኛነቱንም ያረጋግጣል፤

6/ በፋብሪካዎችና በግብዓት አምራቾች መካከል ትስስር እንዲፈጠር ያደርጋል፤

7/ ለሲሚንቶ ምርት በቂ የግብዓት አቅርቦት መኖሩን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል እንዲሁም ተያያዥ ችግሮች ሲፈጠሩ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

cooperate with the concerned authority to take legal actions as needed;

15/ Perform other similar and beneficial functions to the sector.

5. **Regional power and functions**

The Regional Mining Operations Administrative Body shall have the following functions and responsibilities: to

1/ identify the input mineral production areas;

2/ provide license area through contract to a licensee legally established; administer and receive the area when the license expires after terminating the contract;

3/ Monitor the environmental rehabilitation works undertaken by the licensees;

4/ provide training on input production, quality assurance and environmental rehabilitation works;

5/ gather the documents provided by input mineral producers; confirm the authenticity of the files;

6/ create linkages between factories and input mineral producers;

7/ Monitor and supervise the supply of sufficient inputs for cement production and take corrective action in case of associated problems;

8/ በግብአት አቅርቦት እና ስርጭት ላይ ያልተገቡ ተግባራት እንዳይፈፅሙ ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፣ ያስወስዳል፤

9/ በተዘረጉ የግንኙነት ስርዓቶች ግብረ መልሶችን እና ሪፖርቶችን በየወቅቱ ለሚንስቴሩ ያቀርባል፤

10/ በፋብሪካዎች እና በአካባቢያቸው ማህበረሰብ መካከል ሰላማዊ ግንኙነት እንዲኖር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ይሰራል፤

11/ የግብዓት አምራችቾች ምርታማነት እንዲያድግ ድጋፍ ያደርጋል፤ በገቡት የውል ግዴታ እና የስራ ፕሮግራም መሰረት መስራታቸውን ይከታተላል፤

12/ የሲሚንቶ ግብዓት በተተመነበት ዋጋ እንዲሸጥ ክትትል ያደርጋል፤

13/ የግብዓት አምራቾች የስራ አፈጻጸም መረጃዎችን ይገመግማል፤ አስፈላጊ ማስተካከያዎችን ያደርጋል፤

14/ የሲሚንቶ ግብዓት አምራቾች ላይ አስፈላጊውን የክትትል እና የቁጥጥር ተግባራት ያከናውናል፤

15/ በክልሉ የተሰጡ የግብዓት ማምረቻ ቦታዎች የክምችት መጠን ኦዲት ያደርጋል፤ በግኝቱ መሠረት የእርምት እርምጃ ይወስዳል፤

16/ ፋብሪካዎች እና የግብዓት ማዕድናት የሚመረቱበት አካባቢዎች የመሰረተ ልማት እና የሃይል አቅርቦት እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል፤

8/ Control inappropriate activities in relation to input supply and distribution; take measures and cooperate with the concerned authority to take legal actions as needed;

9/ provide periodic feedback and reports to the ministry through communication channels that have been laid out;

10/ Promote good relations among factories, input mineral producers and the local community in cooperation with the concerned bodies;

11/ provide support for input producers to enhance their productivity; monitor their compliance with the terms and conditions of the contract and work program;

12/ supervise cement input minerals to be sold at the rate that have been determined;

13/ evaluate the work performance data of the input producers; carry out the necessary adjustments;

14/ conduct the necessary supervision and control activities on cement input mineral producers;

15/ audit the stock amount of input minerals for the licenses that have been issued by the region; carry out subsequent necessary actions based on the findings;

16/ Create conditions for better infrastructure and power supply in areas where cement and input minerals are produced;

17/ ያለበቂ ምክንያት ከአቅም በታች የሚያመርትን ወይም ማምረት ያቆመን የግብዓት አምራች ባለፈቃድ በመለየት ድጋፍ ያደርጋል፤ አስፈላጊ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፤

18/ በዘርፉ የስራ እድል እንዲፈጠር እና የማህበረሰቡ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ይሰራል፤

19/ ለዚህ መመሪያ አላማዎች መሳካት ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

17/ Provide support to input suppliers that are producing below capacity or ceased production for no apparent reason; undertake corrective measures as necessary;

18/ work to create job opportunities within the sector and to ensure the economic benefit of the community;

19/ Carry out similar activities that are beneficial towards the attainment of the objectives under this directive.

## ክፍል ሦስት

## የግብአት አቅራቢዎች እና የፋብሪካዎች ተግባር እና ሀላፊነት

### 6. ግብዓት አምራች ባለፈቃድ ወጣቶች

የግብዓት አምራች ባለፈቃድ ወጣቶች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፤

1/ ለሁለት አመት ብቻ ለመስራት ግዴታ/ውል ከሚመለከተው አካል ጋር መግባት፤

2/ ውልን ብቻ መሰረት ያደረገ ተግባር ማከናወን፤

3/ ግብዓት በማምረት ሂደት ወቅት ለሚከሰተው የአካባቢ ጉዳት መልሶ የማልማት ስራ ማከናወን፤

4/ ግብዓት ከምርት ቦታ ሲጫን አስፈላጊውን መረጃ በመሰብሰብና በማደራጀት ለፈቃድ ሰጪው አካል በየአስራ አምስት ቀኑ ሪፖርት ማድረግ፤

## Part Three

## Functions and Responsibilities of the Input Suppliers and Factories

### 6. Youth Input suppliers Licensees

Youth Input suppliers licensees have the following functions and responsibilities: to

1/ carry out operations by entering into a contract with the concerned body only for a period of two years;

2/ perform tasks only based on the contract signed;

3/ carry out rehabilitation works on environmental damages that occur during input mineral production process;

4/ Collect, organize and report the necessary information regarding loaded inputs from the production site to the licensing authority every fifteen days;

5/ ቀልጣፋ የግብዓት አቅርቦት ስርዓት መዘርጋትና በውሉ መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ግብዓት ማቅረብ፤

6/ አመታዊ እና ወርሃዊ የምርት ዕቅድን ለፍቃድ ሰጪው አካል አስቀድሞ ማቅረብ፤

7/ የሽያጭ፣ የርክክብ፣ የዋጋ እና ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለፈቃድ ሰጪው አካል ማስተላለፍ፤

8/ አግባብ ባለው አካል ለተመደቡ ተቆጣጣሪዎች አስፈላጊውን የስራ ትብብር ማድረግ፤

9/ የግብዓት አቅርቦት ስርዓቱን የሚያዛቡ ወይም የሚያስተጓጉሉ ማናቸውንም ተግባራት አለመፈፀም፡፡

7. ሌሎች ባለፈቃዶች

ሌሎች የግብዓት አምራች ባለፈቃዶች የሚከተሉት ግዴታዎች አሉባቸው፤

1/ ለራሳቸው ፋብሪካ ከሚያመርቱ ባለፈቃዶች በስተቀር ግብአት ከሚሸጡለት ፋብሪካ ጋር ህጋዊ ውል መዋዋል፤

2/ ቀልጣፋ የግብዓት አቅርቦት ስርዓት መዘርጋትና በገቡት ውል መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ግብዓት ማቅረብ፤

3/ ለሽያጭ የሚያቀርቡትን ግብዓት ሪፖርት ለፍቃድ ሰጪው አካል በየአስራ አምስት ቀኑ የመስጠት፤

4/ ከግብዓት ምርትና አቅርቦት ስራ ጋር በተያያዘ ለሚከሰተው የአካባቢ ጉዳት የመልሶ ማልማት ስራዎችን የማከናወን፤

5/ አመታዊ እና ወርሃዊ የግብአት ምርት ዕቅድ አስቀድሞ ለፈቃድ ሰጪው አካል ማቅረብ፤

5/ establish an efficient input supply system and provide quality inputs in accordance with the contract;

6/ provide in advance annual and monthly production plan to the licensing authority;

7/ transfer sales, delivery, price and other necessary information to the licensing authority;

8/ provide the necessary cooperation to supervisors assigned by the relevant authority;

9/ Refrain from committing actions that disrupt or disturb the input supply system.

**7. Other Licensees**

Other licensees have the following functions and responsibilities: to

1/ except for licensees who produce inputs for their own factory, conclude a contract with the factory to which they sell input minerals;

2/ lay out an efficient input supply system and provide quality inputs in accordance with the contract;

3/ submit report to the licensing authority the input to be sold every fifteen days;

4/ carry out rehabilitation works on environmental damages that occur during input mineral production and delivery process;

5/ provide in advance annual and monthly production plan to the licensing authority;

6/ የሽያጭ፣ የርክክብ፣ የዋጋ እና ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎችን ለፈቃድ ሰጪው አካል ማቅረብ፤

7/ አግባብ ባለው አካል ለተመደቡ ተቆጣጣሪዎች አስፈላጊውን የስራ ትብብር ማድረግ፤

8/ የግብዓት አቅርቦት ስርዓቱን የሚያዛቡ ወይም የሚያስተጓጉሉ ማናቸውንም ተግባራት አለመፈፀም፡፡

**8. ፋብሪካዎች**

ፋብሪካዎች የሚከተሉት ግዴታዎች አለባቸው፤

1/ ለፋብሪካው የሚቀርበውን አጠቃላይ ግብዓት እና የክሊንከር ምርቶች መመዝገብ እና ለፍቃድ ሰጪው አካል ማሳወቅ፤

2/ አመታዊ እና ወርሃዊ የምርት መጠን እቅድ ማሳወቅ፤

3/ የሲሚንቶ ምርት በዓይነት እና በመጠን በየሳምንቱ ለፍቃድ ሰጪው አካል ማሳወቅ፤

4/ የሲሚንቶ የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ በየስድስት ወሩ ማቅረብ፤

5/ የፋብሪካ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ የማምረት አቅም በየሩብ አመቱ ማሳወቅ፤

6/ ሲሚንቶ በሙሉ አቅም ማምረት፣ በአቅሙ ልክ ማምረት የማይችልበት ሁኔታ ሲከሰት በሃያ አራት ሰዓት ውስጥ ለፈቃድ ሰጪው አካል ማሳወቅ፤

7/ ፋብሪካው የተጠቀመውን የግብዓት መጠን እና ሌሎችን ማስረጃዎችን የሚያሳዩ ሰነዶችን ለፈቃድ ሰጪው አካል ማቅረብ፤

6/ provide sales, delivery, price and other necessary information to the licensing authority;

7/ provide the necessary cooperation to supervisors assigned by the relevant authority;

8/ Refrain from committing actions that disrupt or disturb the input supply system.

**8. Factories**

The factories have the following responsibilities to:

1/ register and report to the licensing authority the total amount of input and clinker provided to the factory;

2/ report the annual and monthly production plan to the licensing authority;

3/ report weekly the cement product type and quantity to the licensing authority;

4/ provide cement quality assurance every six months;

5/ report the factory's maximum and minimum production capacity on a quarterly basis;

6/ produce cement at full capacity; notify the licensing authority within twenty-four hours of the occurrence of inability to produce at full capacity;

7/ producing cement and inputs below capacity without sufficient reasons;

8/ አግባብ ባለው አካል ለተመደቡ ተቆጣጣሪዎች አስፈላጊውን የስራ ትብብር ማድረግ፤

9/ የግብዓት እና የሲሚንቶ አቅርቦት ስርዓቱን በማናቸውም መልኩ የሚያዛቡ ወይም የሚያስተጓጉሉ ማናቸውንም ተግባራት አለመፈፀም፡፡

**9. የተከለከሉ ተግባራት**

1/ ያለበቂ ምክንያት ሲሚንቶ እና ግብዓት ከአቅም በታች አለማምረት፤

2/ በማንኛውም መልኩ የሲሚንቶ እና የግብዓት እጥረት በመፍጠር ገበያውን አለማስራብ፤

3/ የሲሚንቶ እና የግብዓት ዝውውርን በማናቸውም መልኩ አለማስተጓጎል፤

4/ አስፈላጊው የይለፍ ፍቃድ ሳይያዝ የሲሚንቶ ግብዓት አለማዘዋወር እና አለመሸጥ፤

5/ አግባብ ባለው አካል ለተመደቡ ተቆጣጣሪዎች ትብብር አለማድረግ፤

6/ ለፈቃድ ሰጪው አካል ሀሰተኛ እና አሳሳች ሪፖርቶችን ማቅረብ፡፡

## ክፍል አራት
## ስለ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

**10. ስለ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃዎች**

1/ የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች በማናቸውም መልኩ በሚተላለፉ ሰዎች ላይ አግባብ ያለው አካል እንደ ጥፋቱ ሁኔታ በሚከተለው ሁኔታ ተመጣጣኝ የሆነ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፤

ሀ/ የሲሚንቶ ግብአት አምራች ሲሆን፤ በማዕድን ስራዎች አዋጅና ደንብ

8/ Depriving the market by creating cement and input shortage by any means.

9/ Disrupting the cement and input circulation process by any means.

**9. Prohibited activities**

1/ producing cement and inputs below capacity without sufficient reasons;

2/ Depriving the market by creating cement and input shortage by any means.

3/ Disrupting the cement and input circulation process by any means.

4/ Transiting and selling cement input minerals without having the necessary permit.

5/ Not cooperating with supervisors assigned by the relevant authority.

6/ Providing false or fraudulent reports to the licensing authority.

## Part Four
## Administrative Actions

**10. Administrative and legal actions**

1/ The relevant authority may take appropriate administrative measures against persons who are in violation of the provisions of this directive as follows;

A. where it is cement inputs licensee, in accordance with the mining operation

ድንጋጌዎች መሰረት እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

ለ/ የሲሚንቶ አምራች ፋብሪካ ሲሆን፤ እንደ ጥፋቱ ክብደት ማስጠንቀቂያ የመስጠት፣ ለጊዜው ስራውን የማስቆም እና ፈቃዱን የመሰረዝ እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

ሐ/ ጉዳዩ የወንጀል ሃላፊነትን የሚያስከትል ሆኖ ከተገኘ በወንጀል ሕጉ መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚወሰድ አስተዳደራዊ እርምጃ በፅሑፍ ሆኖ እርምጃ ለሚወሰድበት አካል መድረስ አለበት፡፡

## 11. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት

1/ በተወሰደበት አስተዳደራዊ እርምጃ ቅሬታ ያለው ማንኛውም ሰው ቅሬታውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ በፅሑፍ ውሳኔውን ለሰጠው ተቋም የበላይ ሃላፊ ማቅረብ አለበት፤

2/ የበላይ ሃላፊው በቀረበው ቅሬታ ላይ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ውሳኔውን ለአመልካቹ በፅሑፍ ማሳወቅ አለበት፤

3/ የበላይ ሃላፊው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን ካላሳወቀ ወይም አመልካቹ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፤

4/ ማንኛውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ለፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ

proclamation and Regulation;

B. where it is cement factory, it will be notified, suspended, or revoke the license based on the weight of the violation;

C. if the case entails criminal liability, such persons may be held accountable under the criminal law.

2/ Administrative measures to be taken in accordance with sub-article 1 of this Article shall be notified to the person in writing.

## 11. Appeal Procedures

1/ Any person aggrieved by an administrative decision shall apply within 10 (ten) working days to the head of the relevant authority in writing.

2/ The head of the relevant authority shall notify the applicant his decision within 10 (ten) working days in writing.

3/ If the head of the relevant authority has not notified his decision within the period specified in sub-article 2 of this Article or if the applicant is aggrieved by the decision, he may appeal to the competent court;

4/ No person may appeal to the competent court in accordance with sub-article 3 of this Article

የሚችለው በውሳኔ ሰጪው አካል ያሉ አስተዳደራዊ መፍትሔዎችን በሙሉ ከተጠቀመ በኋላ ነው፡፡

unless he has exhausted all the administrative remedies within the relevant authority.

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## Part Five
## Miscellaneous Provisions

**12. የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ መመርያ አፈጻጸም ማንኛውም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፤

**12. Obligation to Cooperate**

Any person shall cooperate for the execution of this directive.

**13. መመሪያውን ስለ ማሻሻል ወይም ስለመሻር**

ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ወይም ሊሽረው ይችላል፡፡

**13. Amendment or repeal**

The Ministry may amend or repeal this Directive.

**14. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ነገሮች**

የዚህን መመሪያ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም አሰራር ወይም ልምድ በዚህ መመሪያ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**14. Matters not applicable**

No working procedure or practice shall in so far as they are inconsistent with this Directive, be applicable with respect to matters provided for in this Directive.

**15. መመሪያው ተፈጻሚ የሚሆንበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ፊርማ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**15. Effective Date**

This directive shall enter in to force from the date of approval by the signature of the Minister.

አዲስ አበባ ግንቦት 1 ቀን 2014 ዓ.ም

ታከለ ኡማ (ኢንጂነር)

የማዕድን ሚኒስቴር ሚኒስትር

Done at Addis Ababa, this 9 day of May 2022

Takele Uma (Eng.)

Minister of Ministry of Mines